የማን ባሪያ ነዎት?

ቴዎድሮስ ደመላሽ

የማን ባሪያ ነዎት?

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ያዘጋጀው የኣማርኛ መዝገበ ቃላት ባሪያ የሚለውን ቃል «፣ በጦርነት ላይ እየተማረከ ወይም በገንዘብ እየተገዛና እየተሸጠ ወይም ካለበት አካባቢ በግድ ታፍኖ እየተወሰደ ለማራኪው ወይም ለገዛው ወይም አስገድዶ ለወሰደው ሰው በነጻ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ሰው፡፡ 2. አገልጋይ፣ ታዛዥ፣ ሎሌ፡፡ 3. መብትና ነፃነት የሌለው፣ በተገዥነት የሚኖር ሕዝብ...» በሚል ይፈታዋል (ገጽ 239)፡፡

በዚህ ትርጉም መሠረት ባሪያ የሆነ የእኔ የሚለው መብት የሌለው በመሆኑ እንደ ቁስ በገንዘብ የሚሸጥ ወይም የሚገዛ፣ ያለ ምንም ዋጋ ወይም የላብ ካሳ በነጻ የሚያገለግል፣ መብትና ነጻነት የሌለው ማለት ነው፡፡ ከዚህ ወጣ ተብሎ ሲታይ ደግሞ ባለ ቤቱ (የባሪያው አሳዳሪ) ከወደደ ለሰው በውሰትም ሆነ በስጦታ ሊሰጠው የሚችል ደስ ካለው ሊገድለው አልያም አስሮ ሊያስቀምጠው የሚችለው የግል ንብረቱ ነው፡፡

አንድ ባሪያ የማን «ንብረት» እንደ ሆነ ለማመልከት በገላው ላይ ባለቤቱ የወደደውን ምልክት ሊያደርግበት የሚችል ሲሆን እሱም በሸጠው ሰዓት የገዛው ሰው ሌላ ምልክት በማድረግ የእሱ «ንብረት» መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ማለት በገዛ ገላው ላይ እንኳ መከልከል ስለማይችል ገንዘው የወደደውን ያደርግበታል፡፡ ባሪያው የራሱ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የእኔ የሚለውም ምንም ነገር የለውም፡፡ ሌላው ቢቀር ልጅ ቢወልድ እንኳ ልጁ የባሪያው ሳይሆን የአሳዳሪው «ንብረት» ነው የሚሆነው፡፡ በቤትዎ ያለች በግ ብትወልድ ግለገሊቱን ከፈለጉ በቤትዎ ለማሳደግ አልያም ለወዳጅዎ ለመስጠት ወይም ለመሸጥ ደስ ካልዎትም ለምግብነት ለማቅረብ እንደሚችሉት ማለት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የሁለት ነገሮች ባሪያዎች መሆናቸውን ይናገራል፤ ሰዎቹ ፈቅደውም ይሁን ያለ ፈቃዳቸው ከሁለቱ የአንዱ ባሪያ ናቸው፡፡ ሰዎች ባሪያ የሆኑላቸውን ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ «... ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኀጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ፡፡ ነገር ግን አስቀድማችሁ የኀጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ፥ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ፥ ከኀጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኵስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ

ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ። የኀጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና» በማለት አስቀምጦታል (ሮሜ 6÷16-20)።

የኀጢአት ባሪያ

ሐዋርያው «... [የማደርገውን] የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኀጢአት ነው እንጂ። በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም። የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኀጢአት ነው እንጂ» ይላል። ይህም ክፉኛ የሚያሳስበው ስለሆነ «እኔ ምንኛ ኀስቄላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ሲል ጭንቀቱን ያሰፍራል። ምክንያቱም የኀጢአት ባሪያ ስለሆነ ለእርሱ (ለኀጢአት) የሚገዛ በመሆኑ ኀጢአት እንደወደደ ይመራዋል እንጂ ራሱን መምራት ስላልቻለ (ሮሜ 7÷17-25)።

ኀጢአት ምንድን ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ኀጢአት ለሚለው ቃል «ስሕተት፣ ክፋት፣ ሕግን መተላለፍ፣ ዓመፃ፣ በጎ ማድረግን ዐውቆ አለመሥራት፣ በእምነት መሠረት አለ መኖር፣ ወደ እግዚአብሔር ክብር አለመብቃት» መሆኑን አሳይቷል (ገጽ 133)። ሰዎች ስሕተት ሠሩ ሕግን ተላለፉ፣ ዓመፃ ውስጥ ገቡ... የሚባለው ምን ሲያደርጉ ወይም ምን ሳያደርጉ ሲቀሩ ነው?

- **«በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኀጢአት ነው»** (ሮሜ 14÷23)፤ ምንም እንኳ ሐዋርያው በዚህ ምንባብ ስለ መብልና ስለ መጠጥ እያስተማረ ቢሆንም ሐሳቡን ሲዘጋ ግን ነገሮች ሊደረጉ የሚገባቸው በእምነት መሆኑን በማሳየት ነው። እምነት እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ነገር ሲሆን የእምነት ጉድለት ደግሞ ሐዋርያው እንዳለው ኀጢአት ነው።
- **ትእዛዛቱን አለመጠበቅ፤** እግዚአብሔር አምላክ ሕዝበ እስራኤል ለእርሱ የሚገዙና ፈቃዱን የሚፈጽሙ እንዲሆኑ ሊረዳቸው የሚችል መስመር አስቀምጦ ነበር። ይህም ሕጉ (አስርቱ ትእዛዛት) ነው። ሕጉ ምንም እንኳ በክርስቶስ መምጣት የተፈጸመ ነገር ቢኖረውም (ለምሳሌ ሰንበትን መመልከት ይቻላል) በተሻለ ጠብቆና ጠንክሮ ቀጠለ እንጂ አልተሻረም። ለዚህም ነው ያዕቆብ «ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ፦

አትግደል ብሎአልና፤ ባታመነዝርም፥ ነገር ግን ብትገድል፥ ሕግን ተላላፊ ሆነሃል» የሚለው (ያዕ. 2፡10)። ስለዚህ ኀጢአት መሥራት የማይፈልግ ሰው ሕገ እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

- **በጎ ማድረግ እየቻለ የማይሠራ**፤ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ኀጢአት እንደሠሩ የሚሰማቸው፤ የሰው የሆነ ንብረት ሲወስዱ፣ ውሸት ሲናገሩ፣ ከትዳራቸው ውጪ ወሲባዊ ግንኙነት ሲፈጽሙ፣ ሲገድሉ እና መሰል ድርጊቶችን ሲያደርጉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህ አልፍ ብሎ «በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኀጢአት ነው» በማለት ተገቢ ያልሆነ ነገር መሥራት ብቻም ሳይሆን ተገቢ የሆነ ነገር ሊያደርግ የሚገባው ሆኖ ሳለ የማያደርግም ኀጢአት የሠራ መሆኑን ማወቅ አለበት ይላል (ያዕቆብ 4፡17)።

ከዚህ በላይ የሰፈሩት ኀጢአት ተሠራ የሚባለው ምን ሲደረግ ነው? የሚለውን ቢያሳይ በሚል የቀረበ ጥቅል ማሳያ ነው። እዚህ ውስጥ ኀጢአት ተብለው የሚታወቁት ነገሮች እያንዳንዳቸው ተዘርዝረው አልቀረቡም። ምክንያቱም ከእነዚህ በአንዱ ውስጥ ይካተታሉ ተብሎ ስለታመነ ነው።

ሰዎች የኀጢአት ባሪያ ከመሆን እንዴት ሊድኑ ይችላሉ?

ይህ በሰው የሚቻል አይደለም፤ ቀደም ሲል የቀረቡት ነገሮች (በእምነት መኖር፣ ሕግጋቱን መጠበቅ፣ በጎ ማድረግ) ሁሉም ሰው ሊያደርገው የሚፈልገው ነው። ክፉ መሆን የሚፈልግ ሰው የለም፤ እንዲሁም ደግሞ ከእምነት መጣት የተነሣ ከእግዚአብሔር መንግሥት ብጉድልም ችግር የለም የሚል ሰው አይኖርም። ሐዋርያው «የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም» በሚል እንዳሰፈረው ሆኖብን እያደረግን ያለነው ክፉ እንደ ሆነ ብናውቅም ግን ለመተው ተስኖን እንገኛለን።

እንዴት ነው ነጻ መውጣት የምንችለው? የሚል ጥያቄ ቢነሣ ለዚህ ጥያቄ ሐዋርያው ጳውሎስ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና» በሚል መልስ ይሰጣል (ሮሜ 8፡1-2)። ይህ ማለት ከዚህ በኋላ የጽድቅ ባሪያዎች ሆነናል ማለት ነው።

የጽድቅ ባሪያዎች

ራሳቸውን በፈቃዳቸው ለጽድቅ ባርነት ኣሳልፈው የሰጡ ሰዎች ሁሉ ነገራቸው በጽድቅ የሚሆን በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ፍሬ ብሎ የሚጠራቸው «ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት» ይታይባቸዋል (ገላትያ 5፡22)። እነዚህ «የመንፈስ ፍሬዎች» የሚታዩባቸው ሰዎች ከኀጢአት ባርነት ነጻ ወጥተው ወደ ጽድቅ ባርነት የተሻገሩ በመሆናቸው «ከኀጢአት ኣርነት ወጥታችሁ ለእግዚኣብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ ኣላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው» ሊባሉ ተገብቷቸዋል (ሮሜ 6፡22)

የጽድቅ ባርያ ለመሆን ምን ማድረግ አለብን?

- **«ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና»** (ሮሜ 3፡28)፤ ቀደም ሲል የሰው ልጅ ኀጢአት ሠራ የሚባለው፤ በሚል ከቀረቡት ዝርዝሮች ሕግጋቱን አለመጠበቅ መሆኑ ቀርቦ ነበር፡፤ ነገር ግን ሕግጋቱን ጠብቀው ጻድቅ እንደ ሆኑ የተነገረላቸው በአንድ ወይም በሌላ በደል ውስጥ ወድቀው ተገኝተው የነበሩ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ጽድቃቸው ሙሉ የሆነ ወይም መንግሥተ እግዚአብሔርን እንዲወርሱ የሚረዳ አልነበረም። የሰው ልጆች ከኀጢአት የጸዳና እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ሕይወት እንዲኖሩ ሕግን መጠበቅ ሳይሆን በእምነት መመላለስ ነው የሚጠበቅባቸው። «ያለ እምነትም [እግዚአብሔርን] ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው (ዕብራውያን 11፡6)።
- **«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኀጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው»** (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)፤ እኛ ጽድቅ እንድንሆን የተከፈለ ዋጋ ወይም የተሠራ ሥራ አለ። ቀደም ሲል እንደተባለው በማመን የሚገኝ ጽድቅ አለ ማለት ማመን የሚገባን ነገር አለ ማለት ነው። ኀጢአተኞች የነበርንና ከበደላችን የተነሣ ሞት የሚገባንን እኛን ጽድቅ እንድንሆን ስለ እኛ ኀጢአት የሆነ አካል አለ።
- **«አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን»** (ሮሜ 5፡9)፤ በደለኞች የነበርን እኛን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን

ምን አደረገልን? ቢባል በዚህ ምንባብ «በደሙ» እንደጸደቅን በመናገር ልባችንን ያሳርፍልናል፤ መጽሐፍ ቅዱስ «እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም» ይላልና (ዕብራውያን 9፡22)። በደሙ ያጸደቀን ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ማመን የሚገባንና የጽድቅ ባሪያ መሆን የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።

የማን ባሪያ ነዎት?

የጎጢአት ባሪያ ነዎት ወይስ የጽድቅ? ምናልባት የጎጢአት ባሪያ ሆነው ከሆነ አሁን ምርጫዎትን ማስተካከል የሚችሉበት ሰዓት ላይ ነዎት። ከዚህ በፊት በነበርዎ ሕይወት እግዚአብሔርን ባሳዘኑበት ሁሉ ንስሐ በመግባት ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን ይፈጽሙና አካሄድዎን ከእግዚአብሔር ጋር ያድርጉ። ከዚያም በቀሪ ዘመንዎ ከጎጢአት ባርነት ነጻ ወጥተው የጽድቅ ባሪያ በመሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመመላለስ ራስዎን ለጽድቅ ያስገዙ።

«አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ፤ ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ» (መዝሙረ ዳዊት 142÷10)